**Hallo
Basel-Stadt**

Kanton Basel-Stadt

# ሊታወቅ የሚገባው

የመጀመሪያ ደረጃ
ክፍት የስራ ሰዓቶች / በዓላት
የመኖሪያ ፈቃድ እና ዜግነት መቀየር
የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ
አልኮል/ ትምባሆ /አደንዛዥ ዕጽ
የቤት እንስሳዎች
አብሮ መኖር በስዊዘርላንድ

# የመጀመሪያ ደረጃ

በKanton Basel-Stadt ለከተማው አዲስ ነዎት? አዲስ ከሆኑ በ14 ቀናት ውስጥ በነዋሪዎች ምዝገባ ቢሮ መመዝገብ አለብዎት። የነዋሪዎች ምዝገባ ቢሮ ለምዝገባ በአካል በሚቀርቡበት ግዜ ለአዲስ ነዋሪዎች የእንኳን ደህን መጡ አቀባበል ገለጻና ንግግር ያደርጋል።

## ኦፊሻላዊ ምዝገባ

ወደ Kanton Basel-Stadt ካንቶን ለመኖር የመጡ አዲስ የሆኑ ሰዎች በ 14 ቀናት ውስጥ አዲስ በሚኖሩበት መኖሪያ ቦታ በሚገኝ በነዋሪዎች ምዝገባ ቢሮ (Basel, Riehen ወይም Bettingen) መመዝገብ አለባቸው።
ከስዊዘርላንድ ወይም ከአውሮፓ ህብረት ወይም ከአንዱ /EFTA/ከአውሮፓ ነጻ የንግድ ቀጠና ማህበር አገር ከሆኑ፣
በጽሑፍ ወይም በ E-Umzug CH/ምዝገባ በኤለክትሮኒክ መንገድ/ ወይም Basel-Stadt, Riehen oder Bettingen በሚገኙ በነዋሪዎች ምዝገባ ቢሮ በአካል ቀርበው መመዝገብ ይችላሉ። ከአውሮፓ ህብረት ወይም ከአንዱ /EFTA /ከአውሮፓ ነጻ የንግድ ቀጠና ማህበር አገር ካልሆኑ ግን፣ እባክዎን ወደ ነዋሪዎች ምዝገባ ቢሮ (Einwohneramt) ወደ Spiegelhof የደንበኞች ማዕከል ይምጡ። እዛም ባዮሜትሪክ መረጃዎ መመዝገብ አለበት። ለምዝገባ ያስከፍላል።
የመመዝገቢያ አድራሻው እንደሚከተለው ነው።
Kundenzentrum Spiegelhof
Spiegelgasse 6
4001 Basel
Tel. 061 267 70 60
ለመመዝገብ ምን ያስፈልጎታል? ምን ዓይነት ሰነድ ይዘው መቅረብ እንዳለብዎት እባክዎን አስቀድመው ስለሁኔታው በደንብ ይረዱ። የሚያቀርቧቸው ሰነዶች በጀርመንኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በጣልያንኛ ወይም ከሆኑ ተቀባይነት አላቸው።
ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሰነዶች የግድ አስፈላጊ ናቸው፣

- የመመዝገቢያ ፎርም (Anmeldeformular). የመመዝገቢያ ፎርም አስቀድመው መሙላት አለብዎት።
- ጊዜው ያላለፈበት (ለEU/EFTA) የሚያገለግል የጉዞ ፓስፖርት ወይም የመታወቂያ ወረቀት ከለር ኮፒ
- የቤት ኪራይ ውል ወይም የመኖሪያ ካርድ ኮፒ

ለማንኛውም በተጨማሪ እነዚህ ሰነዶች ያስፈልጎት ይሆናል፣

- ቪዛ
- የስራ ውል
- የወንጀል ሪከርድ መግለጫ
- የጋብቻ ሰርተፊኬት
- እና ሌሎች ተጨማሪ ሰነዶች

በአንድ ካንቶን ውስጥ የቤት አድራሻዎትን ቢቀይሩ ወይም ከባዝል ከተማ ቢቀይሩ፣ የነዋሪዎች ምዝገባ ቢሮ ሄደው መመዝገብና ማስታወቅ አለብዎት።
ከአውሮፓ ህብረት ወይም ከአንዱ /EFTA/ ከአውሮፓ ነጻ የንግድ ቀጠና ማህበር አገር ካልሆኑ፣ ሆኖም ግን ስዊርላንድ ውስጥ ነዋሪ ከሆኑ፣
ከአንድ ካንቶን ወደ ሌላ ካንቶን ከመቀየርዎ በፊት አስቀድመው የካንቶን Basel-Stadt የኢሚግሬሽን ቢሮ የስምምነት ፍቃድ መስጠት አለበት። መመዝገብ የሚቻለው ፍቃድ ካገኙ በኋላ ነው።

## የአቀባበል ንግግር

ለምዝገባ ወደ የነዋሪዎች ምዝገባ ቢሮ በሚሄዱበት ግዜ በአካል፣ ንግግርና ቃለ መጠይቅ እንደሚኖር ይገንዘቡ። ሰላም እንሎታለን፣ ለጥያቄዎችዎም መልስ እንሰጣለን እንዲሁም ስለ ባዝል ሕይወት እንገልጽሎታለን።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gut-zu-wissen/erste-schritte

# ክፍት የስራ ሰዓቶች / በዓላት

**ከባቡር ጣቢያዎች ወይም ከነዳጅ ማደያዎች በስተቀር፣ በስዊዘርላንድ አብዛኛዎቹ ሱቆች እሁድ ዝግ ናቸው። ህዝባዊ በዓላት የሚወሰኑት በካንቶኖች ነው።**

## በዓላት

ህዝባዊ በዓላት በሰራተኛ ህግ ላይ የተደነገጉ ሲሆን በሕጉ መሰረት ልክ እንደ እሁድ የእረፍት ቀን ናቸው። ነሐሴ 1 (ብሄራዊ በዓል) በመላው ስዊዘርላንድ ህዝባዊ በዓል ነው። በተጨማሪም እያንዳንዱ ካንቶን ተጨማሪ ኦፊሻላዊ በዓላትን ማጽደቅ ይችላል። በካንቶን Basel-Stadt የሚከተሉት ቀናት በዓላት ናቸው። አዲስ አመት (ታህሳስ 1) ፣ ስግደት (ቅድመ ፋሲካ ዓርብ)፣ ፋሲካ፣ የሰራተኞች ቀን (ግንቦት 1) ፣ እርገት (ከፋሲካ ከ40 ቀን በኋላ ሐሙስ)፣ የመንፈስ ቅዱስ ቀን /ፌንግስተን/፣ ብሄራው በዓል (ነሐሴ 1)፣ ገና (ታህሳስ 25)፣ የእስጢፋኖስ ቀን (ታህሳስ 26).

## የገበያ ሱቆች የሚከፈቱበት ሰዓት

የገበያ ሱቆች የመክፈቻ ሰዓታት በየካንቶኑ ይለያያሉ። በካንቶን Basel-Stadt ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 6.00 እስከ ምሽቱ 20.00 ሰዓት ድረስ ሱቆች መክፈት ይችላሉ። የመክፈቻ ግዜውና ሰዓቱ እንደየሱቁ ይለያያል፣ ሊያጥርም ሊረዝምም ይችላል። አብዛኛዎቹ ሱቆች ቅዳሜ ከሌሎቹ ከሳምንቱ ቀናት አስቀድመው ብዙውን ግዜ በ18.00 ሰዓት ይዘጋሉ። እሁድ ግን አብዛኛዎቹ ሱቆች ዝግ ናቸው። ልዩነቱ በባቡር ጣቢያዎች፣ በነዳጅ ማደያዎች ወይም የሰፈር ውስጥ ሱቆች በተለምዶ ለ7 ቀናት ክፍት ሲሆኑ፣ ከሌሎቹም ሁሉ ቀድመው የሚከፍቱ እና ዘግይተው የሚዘጉ ናቸው።

## የአስተዳደር ጽ/ቤቶች ክፍት የስራ ሰዓቶች (DE)

በህጉ መሰረት የካንቶን አስተዳድር ጽ/ቤቶች ከሰኞ እስከ ዓርብ ከጥዋቱ 8.00 እስከ ቀትር 12.00 እንዲሁም ከ14.00 እስከ 17.00 ሰዓት ክፍት ናቸው። አንዳንድ ጽ/ቤቶች ከሰዓት ከኋላ ከ13.30 በኋላ ይከፍታሉ፣ ወይም በስልክ ከዚያም በላይ አገልግሎት ይሰጣሉ። አስቀድሞ በኢንተርኔት ወይም በስልክ ቢሮው መቼ ክፍት እንደሚሆን መጠየቅ ይመከራል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gut-zu-wissen/oeffnungszeiten--feiertage

# የመኖሪያ ፈቃድ እና ዜግነት መቀየር

**በስዊዘርላንድ ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ለመኖር ወይም እዚህ ለመስራት ፈቃድ ያስፈልጋል። የተለያዩ ዓይነቶች የመቆያ ፈቃዶች እና የመኖሪያ ፈቃዶች መካከል ብዙ ልዩነት አለ።.**

## የፈቃድ ዓይነቶች

በስዊዘርላንድ በስራ ላይ ያለ ወይም ከ3 ወር በላይ ቆይታ ላደረገ ሰው የመቆያ ፍቃድ ያስፈልገዋል። ይህም ፍቃድ ከካንቶን የስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt) ይሰጣል። በአጭር የመቆያ ፍቃድ (እስከ 1 ዓመት)፣ በመቆያ ፍቃድ (የተገደበ) እና በመኖሪያ ፈቃድ (ያለ ገደብ)፣ እንዲሁም ድንበር የማቋረጥ ፍቃድ መካከል ልዩነት አለ።

- „ለአጭር ጊዜ የመቆያ ፍቃድ L“ (Kurzaufenthaltsbewilligung L): ይህ ፈቃድ የሚሰጠው ለተገደበ ግዜ (በብዛት ለ1 ዓመት) ለተወሰነ የመቆያ ምክንያት ስዊዘርላንድ ለመኖር ያስችላል። አብዛኛዎቹ ከ EU-/EFTA ሃገር የመጡ ነዋሪዎች ከ 3 ወር እስከ 1 ዓመት ድረስ ስራ (የስራ ውል) ያላቸው መሆኑ ማረጋገጥ ከቻሉ፣ ይህ ፍቃድ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው።
- „የመቆያ ፍቃድ B“ (Aufenthaltsbewilligung B) (እስከ 1 ዓመት): ይህ ፈቃድ የሚሰጠው ለረጅም ጊዜ ስዊዘርላንድ ለሚቆዩ ሰዎች ነው። አብዛኛዎቹ ከ EU-/EFTA ሃገር የመጡ ነዋሪዎች ከ1 ዓመት በላይ ስዊዘርላንድ ውስጥ የሰሩ መሆኑን ማረጋገጥ ከቻሉና (የስራ ውል) ካላቸው፣ ይህንን ፈቃድ የማግኘት መብት አላቸው። ይህ ፈቃድ ከEU/EFTA ለመጡ ነዋሪዎች ለ 5 ዓመት ይሰጣል። ከዚህ ውጪ ከሌላ አገር ለመጡ ሰዎች ግን ለ1 ዓመት የሚቆይ ብቻ ነው የሚሰጣቸው። ከዛ በኋላ ለማራዘም ማመልከት ያስፈልጋል። ይህ ፈቃድ እንዲራዘም ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌ ያህል የጀርመን የቋንቋ ኮርስ ከመማር ጋር ይያያዛል። ካልሆነ ግን የማራዘም መብት የለዎትም። ሊራዘም ከማይችልባቸው ምክንያቶች ይህል፣ ለምሳሌ የወንጀል ቅጣት ወይም የሶሻል ድጋፍ ጥገኛ ከሆኑ ላይራዘም ይችላል። ያለማቋረጥ ከ6 ወር በላይ የውጭ አገር ቆይታ ካደረጉም ይህ የመቆያ ፈቃድ የአገልግሎት ግዜው ያበቃል። የስደተኝነት ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያገኙ ስደተኞችም ፈቃድ B ይሰጣቸዋል።
- „የመኖሪያ ፈቃድ C“ (Niederlassungsbewilligung C): ይህ ፈቃድ የሚሰጠው ስዊዘርላንድ ውስጥ ከ5 ወይም 10 ዓመት በላይ ለቆዩ ነው። በተለይ ደግሞ ከEU/EFTA ሃገራት እንዲሁም ከሌሎች ሶስተኛ ሃገራት ለመጡ ነዋሪዎች የተለያዩ መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ወደ ሌላ የውጭ አገር ቢሄዱ የተሰጠዎት የመኖሪያ ፈቃድ. እንደየሁኔታው ቢበዛ ለአራት ዓመት መቆየት ይችላል። ይህ እንዲሆን ግን በስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት Migrationsamt ማመልከት ያስፈልጋል።
- „ጊዝያዊ መቀበያ ፍቃድ F“ (Vorläufige Aufnahme F): ይህ ፈቃድ የሚሰጣቸው የስደተኝነት ጥያቄ ላመለከቱ ስደተኞች ሲሆን፣ እንደ ስደተኝነት ተቀባይነት ላላገኙ ስደተኞች ነው፣ ሆኖም በግዚያዊነት ለተመዘገቡት የሚሰጥ ፈቃድ ነው። ይህም ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት።

## የውጪ አገር ዜጋ መታወቂያ

በስዊዘርላንድ የሚኖሩ የውጪ ዜጋዎች የውጪ አገር ዜጋ (Ausländerausweis) መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ይሰጣቸዋል። የሚሰጠው የመታወቂያው ዓይነት በተለያዩ መስፈርቶች ይወሰናል። ከውጭ አገር ወደ ጀርመን የሚመጡ ሰዎች የክሬዲት ካርድ ዓይነት ቅርጽ ያለው የባዮሜትሪክ መታወቂያ ካርድ ይሰጣቸዋል። በምዝገባው ግዜ የጣት አሻራቸው እንዲሁም የፎቶ ምስላቸው ይወሰዳል። መታወቂያቸው ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ወድያውኑ በቅጽበት የግድ ለፖሊስ ማመልከት ያስፈልጋል። የጠፋብዎት መሆኑን ፖሊስ ያመለከቱበትን የምዝገባ ፎርም ማረጋገጫ እንዲሁም የአገርዎን የፓስፖርት ቅጂ ወይም (የEU/EFTA) ዜጋ ከሆኑ የመታወቂያ ወረቀትዎን በመያዝ አዲስ የመታወቂያ ወረቀት በስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt) ማመልከትና ማዘዝ ይችላሉ።

## ማራዘም

እንደ የመቆያ/የመኖሪያ/ ፈቃዱ ዓይነት እና እንዲሁም እንደ ዜግነትዎ ዓይነት እንደየሁኔታው በተለያየ ጊዜ የመቆያው /የመኖሪያው/ ፈቃዱ መራዘም አለበት። መራዘም ካለበት የማራዘሚያ ቅጽ /የማለቂያ ጊዜ ማሳሰቢያ/ (Verfallsanzeige) ይደርስዎታል። በዚህ በተላከሎት ቅጽ ላይ የስራ ቀጣሪዎ ማረጋገጥና መሙላት አለበት፣ በመጨረሻም የአገርዎ የጉዞ ፓስፖርት ቅጂ ወይም (የEU/EFTA) ዜጋ ከሆኑ የመታወቂያ ወረቀትዎን ከቅጹ ጋር በማያያዝ ለስደተኞች አስተዳደር ጽ/ቤት (Migrationsamt) መላክ አለብዎት።

## በደንቡ መሰረት ዜግነት መቀየር

በስዊዘርላንድ ውስጥ ለአሥር ዓመታት የኖረ ማንኛውም ሰው ለፌዴራል የዜግነት ፈቃድ ዜግነት እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል። ከ8 ዓመት ዕድሜው እስከ 18 ዓመት ዕድሜው ድረስ ስዊዘርላንድ ውስጥ የኖረ ማንኛውም ሰው የኖረበት ግዜ እጥፍ ሆኖ ይቆጠርለታል። ዜግነት ለማግኘት ተጨማሪ አስፈላጊ የሆኑ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፣ የመኖሪያ ቦታ ገደብን ማሟላት፣ የጀርመንኛ ቋንቋ በቂ ችሎታ መኖር፣ ከማህበረሰቡ ጋር በጥሩ ሁኔታ መወሃሃድ እና ከዕዳ ነጻ መሆን ወይም ከወንጀል መዝገብ ነጻ መሆን ይጠበቅብዎታል።

## በቀለለ መንገድ ዜግነትን መቀየር

በቀለለ መንገድ ዜግነትን ለመቀየር የተወሰኑ የህግ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፣ ከስዊዘርላንድ ዜጋ ጋር ጋብቻ የፈጸመ የውጭ ዜጋ እንዲሁም ከወላጆቹ አንዱ የስዊዘርላንድ ዜጋ ከሆነ ሰው የተወለደ ልጅ በቀላሉ ዜግነትን መቀየር ይችላል። በቀለለ መንገድ ዜግነትን ለመቀየር መወሰን የሚችለው የፌደራል መንግስቱ ብቻ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gut-zu-wissen/aufenthaltstitel

# የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ

ማንኛውም ዓዋቂ ሰው የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ቢኖረው መልካም ነው። ይህንን ኢንሹራንስ የገባው ሰው፣ ሆን ብሎ ሳይሆን በአጋጣሚ ጉዳት ቢያደርስ፣ ኢንሹራንሱ ወጪውን ይሸፍናል።

## የግል ተጠያቂነት

አንድ ሰው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ ወይም የሌላ ሰው የሆነ ንብረት ቢያበላሽ፣ ይህ ሰው በግሉ በገንዘብ ተጠያቂ ይሆናል። የደረሰውን ጉዳት ሆን ብሎ እንኳን ባይፈጸም፣ ይህ ሰው ተጠያቂ ይሆናል። ክፍያው በጣም ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል በበረዶ ላይ መንሸራተት ስፖርት የሆነ ሰው ላይ ጉዳት ቢደርስበት፣ ጉዳቱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ፍራንክ ሊደርስ ይችላል።

## የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ

አደጋ በሚደርስበት ግዜ የገንዘብ ችግር/ዕዳ/ ውስጥ ላለመግባት፣ የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ (Privathaftpflichtversicherung)መግባት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ አብዛኞቹ የግል ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ይህንን አገልግሎት እንደሚሰጡ ያሳውቃሉ። አብዛኛውን ግዜ በአንድ ቤት ውስጥ በህብረት የሚኖሩ ሰዎች በአንድ ላይ የጋራ የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ውል መፈጸም ይችላሉ። ይህንን ኢንሹራንስ መግባት ግን ግዴታ አይደለም፣ ይሁን እንጂ አጥብቆ ይመከራል።

## ኢንሹራንሱ ምን ይሸፍናል

ኢንሹራንስ የገባው ሰው በሌላ ሰው ንብረት ላይ እና በሰው ላይ አደጋ ቢያደርስ፣ የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንሱ ወጪውን ይሸፍናል። የሚሸፈነው ወጪ የጥገና ወጪዎችን፣ የህክምና ወጪዎችን፣ ለደሞዝ ኪሳራ ማካካሻ ወይም የአካል ጉዳት ካሳዎችን ያካትታል። የግል የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንሱ የተወሰኑ የቤት እንስሳዎች የሚያደርሱት ጉዳቶችን ኪሳራም ወጪ ይሸፍናል። አንድ ቤት ውስጥ በጋራ አንድ ላይ ከሚኖሩት ሰው ላይ ጉዳት ቢደርስ ኢንሹራንሱ የጉዳቱንና የኪሳራውን ወጪ አይሸፍንም። ኢንሹራንሱ ከማይሸፈኑናቸው ጉዳቶች መካከል፣ ጉዳቱ ሆን ተብሎ ከተፈጸመ ወይም በግድየለሽነት አደጋው የደረሰ እንደሆነ ነው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gut-zu-wissen/private-haftpflichtversicherung

# አልኮል/ ትምባሆ /አደንዛዥ ዕጽ

**አደንዛዥ ዕጽ ተይዞ የተገኘ፣ ተጠቃሚ የሆነ ወይም ሲሸጥ የተገኘ ሰው በህግ ይቀጣል። አልኮል እና ትምባሆ ለመገበያየት የዕድሜ ገደብ አለው።**

## አደንዛዥ ዕጽ

በሕግ ያልተፈቀደ አደንዛዥ ዕጽ ይዞ መገኘት፣ መሸጥና መጠቀም በሕግ ያስቀጣል። አነስተኛ መጠን ቢሆንም እንኳን ያስቀጣል። የትኞቹ ንጥረ ነገሮች ሕገ-ወጥ እንደሆኑ በአደንዛዥ ዕጽ ሕግ (Betäubungsmittelgesetz) ላይ ተደንግጓል። በንግድ መልክ አደንዛዥ ዕጽ መሸጥ ከፍተኛ ቅጣት ያስቀጣል።

## አልኮል እና ትምባሆ

አልኮል እና ትምባሆ ለመገበያየት የዕድሜ ገደብ አለው። የትንባሆ ውጤቶችን እና አልኮላዊ መጠጦችን Basel-Stadt ካንቶን ውስጥ ለልጆች እና ዕድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች ለሆናቸው ወጣቶች መሸጥ ክልክል ነው። አንዳንድ እንደ ስፕሪቶዞ /Spirituosen/ ያሉ አልኮላዊ መጠጦች ለነዚህ ዓይነት መጠጦች የዕድሜ ገደቡ 18 ዓመት ነው።

## የማጨስ እገዳ

ስዊዘርላንድ ውስጥ ያሉ ካንቶኖች የማጨስ እገዳን በሚመለከት የተለያየ ሕግ አላቸው። የካንቶን Basel-Stadt የማያጨሱ ሰዎችን ደህንንነት ለመከላከል ሲባል፣ እገዳው በፌደራላዊ ሕግና በካንቶኑ የመስተንግዶ ሕግ / Gastgewerbegesetz/ ላይ የተመሰረተ ነው።
ማጨስ የተከለከለባቸው ቦታዎች፣

- ለህዝብ ክፍት የሆኑ ቦታዎች፣ ህዝብ በሚበዙበት ቦታዎች (የህክምና ቦታዎች፣ የአስተዳደር ጽ/ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ ሙዚየሞች፣ ሲኒማ ቤቶች፣ ቲያትር ቤቶች፣ ባቡሮች እና አውቶቡሶች፣ ሱቆች እና የገበያ ማዕከሎች).
- በአንድ ላይ በጣም ብዙ ሰዎች የሚሰሩባቸው ቦታዎች፣

ሪስቶራንት ውስጥ ማጨስ መቻሉ ወይም አለመቻሉ፣ የሪስቶራንቱ ትልቅነት ነው የሚወስነው። አንዳንድ ሪስቶራንቶች ለሲጋራ አጫሾች የተለየ የማጨሻ ክፍሎችና ቦታዎች አላቸው።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gut-zu-wissen/alkohol--tabak--drogen

# የቤት እንስሳዎች

የቤት እንስሳ የሚያኖር ሰው፣ የተለያዩ ሕጎችን ማክበር አለበት። ለምሳሌ አንዳንድ የእንስሳት ዝርያዎች በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ ሊቀመጡ አይችሉም። ውሻዎች የካንቶኑ ውስጥ መመዝገብ አለባቸው።

## የቤት እንስሳ ማኖር

በኪራይ ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው፣ ጥቃቅን እንስሳዎች እንደ ጊኒ አሳማ፣ ሃምስተር /ትንሽ አይጥ/፣ የካናሪያ ወፎች ወይም አሳዎች የመሳሰሉ ማኖር ይፈቀድለታል። ነገር ግን በኪራይ ውል ውስጥ ትላልቅ እንስሳትን ማኖርና ማቆየት (ድመቶችን ወይም ትናንሽ ውሻዎችን ጭምር) ክልክል ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ጫጫታ የሚፈጥሩ እንስሳት ወይም አደገኛ የሆኑ እንስሳትን በሚመለከት የቤት አከራዩ መከልከል ይችላል። በተጨማሪም የእንስሳት ባለቤቶች የእንስሳት ጥበቃ ሕጎችን ማክበር አለባቸው። ለምሳሌ አንዳንድ እንስሳቶች ለብቻቸው መሆን የሌለባቸው እንስሳት ብቻቸውን ማኖር አይፈቀድም (ለምሳሌ ያህል ጥንቸል)።. እንዲሁም የኬጅ/የእንስሳት ጎጆ/ መጠን እና መሳሪያዎችን በሚመለክት አነስተኛ መስፈርቶች አሉ።. ብዙ እንስሳት (ብርቅዬ እንስሳት) ወደ ስዊዘርላንድ እንዲገቡ አይፈቀድም። በተረፈ ለሌሎች እንስሳት የእንስሳት ህክምና ተቋም ልዩ ፈቃድ ያስፈልጋል።

## ውሻዎች

በBasel-Stadt ካንቶን ውስጥ ልዩ የውሻ ሕግ አለ። የውሻ ባለቤቶች ያለባቸውን ግዴታ በሚመለከት ሕጉ ላይ ሰፍሯል። ተጨማሪ መረጃ የእንስሳት ሃኪም ማግኘት ይቻላል።

- በስዊዘርላንድ ውሻዎች ማይክሮ ቺፕ ሊኖራቸው ይገባል። ይህም በዳታ ባንክ መስፈር አለበት። ውሻው (የክሬዲት ካርድ ቅርጽ ያለው) የውሻ መታወቂያ ይሰጠዋል። ይህም ከትውልድ አገር መታወቂያ ጋር፣ ማለትም አንድን እንስሳ ወደ ኤውሮጳ ህብረት አገሮች ማጓጓዝ ከሚያስችለው መታወቂያ ጋር ተመሳሳይ አይደለም።

- ውሻዎች በካንቶን መመዝገብ አለባቸው፣ ይህንን በሚመለከት ኦን ላይን ላይ የመዝገቢያ ቅጽ አለ። በየዓመቱ ግብር መከፈል አለበት። በተጨማሪም ውሻን ለማኖር ለእያንዳንዱ ውሻ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ (Haftpflichtversicherung) መግባት ግድ ይላል።
- ሁሉም የውሻ ባለቤቶች የውሻቸውን ሰገራ የማንሳት እና የማስወገድ ሃላፊነት አለባቸው። ይህንን ያልፈጸመ፣ መቀጮ ይቀጣል።
- አንዳንድ የውሻ ዘሮች ልዩ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል። (ለምሳሌ ፒትቡል ወይም ሮትቫይለር).
- ውሻዎች በከተማ መናፈሻዎች እና በልጆች መጫወቻ ሜዳዎች ውስጥ በአጠቃላይ መግባት አይፈቀድም።

በካንቶኑ ካርታ "Mapserver" ላይ የውሻዎች ነጻ የመጫወቻ ዞኖች እና የውሻ መታጠቢያ ቦታዎች ምልክት ተደርጎባቸዋል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gut-zu-wissen/haustiere

# አብሮ መኖር በስዊዘርላንድ

**እያንዳንዱ አገር ለየት የሚያደርገው የራሱ የሆነ ባህል አለው። ስዊዘርላንድ ውስጥም ከህብረተሰቡ ጋር እንዴት ተግባብቶ መኖር ማወቅ ያለብዎት ነገር አለ። በስዊዘርላንድ ውስጥም ተግባብቶ ለመኖር እንዲቻል ማወቅ ያለብዎት አንዳንድ ስነ ምግባሮች አሉ።**

## የተለያዩ ዓይነት ባህሎች

ስዊዘርላንድ ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ባህሎችና አስተሳሰቦች አሉ። ይህም አገሪቱ ውስጥ ባሉት አራት ብሔራዊ ቋንቋዎች ላይ የተመረኮዘ ነው። ጀርመንኛ ተናጋሪ በሆኑ የስዊዘርላንድ ቦታዎች የተለመደው ነገር፣ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ከሆኑ የስዊዘርላንድ ቦታዎች ፈጽሞ የተለየ ሊሆን ይችላል። በከተሞችና በገጠር መካከልም ትልቅ ልዩነቶቹ ሊኖሩ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በመላው ስዊዘርላንድ ተመሳሳይ የሆኑ ባህሎች አሉ።

## የሰላምታ አሰጣጦች

ስዊዘርላንድ ውስጥ እንደሚከተለው ሰላም እንባባላለን። አብዛኛውን ግዜ በመጨባበጥ ሰላም እንባባላለን። ሰላም በምንባባልበት ግዜም ዓይን ለዓይን እንተያያለን። በባዝል "Griezi" እንላለን። በጣም የሚተዋወቁ ሰዎች "Sali" ወይም "Hoi"ይባባላሉ። ከከተማ ውጪ ገጠር አካባቢ ሰዎች መንገድ ላይ ሲገናኙ፣ ባይተዋወቁም እንኳን ሰላምታ ይለዋወጣሉ።
ትህትና ስዊዘርላንድ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህም የተነሳ አብዛኛውን ግዜ አመሰግናለሁ "Danke" እና እባክህን Bitte"እንላለን። ለምሳሌ ገበያ ውስጥ ወይም ሪስቶራንት ውስጥ በተደጋጋሚ "Danke" እና "Bitte"እንባባለለን።

## ቀጠሮ ማክበር

ስዊዘርላንድ ውስጥ ቀጠሮ ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው፣ በተለይ ደግሞ በስራ ቦታ ላይ። ከ5 ደቂቃ በላይ ዘግይተው የሚመጡ ከሆነ፣ አስቀድመው ማሳወቅ አለብዎት። ከሰው ጋር መገናኘት ይፈልጋሉ? ከፈለጉ አስቀድመው ቀጠሮ ይያዙ።

## ቀጥታዊ ያልሆነ ግንኙነት

አብዛኛውን ግዜ ስዊዘርላንድ ውስጥ ትችትን በቀጥታ አንገልጽም። ብዙውን ግዜ በመላ ፍንጭ ነው የምንሰጠው። ቢሆንም ትችታችንን ሰዎች በሚረዱት መልክ አድረገን ነው የምንገልጸው። የጀርመንኛ ቋንቋ በቂ የሆነ ዕውቀት ከሌለዎት፣ ለርስዎ በተለይ ሁኔታውን ለመረዳት በጣም ይከብዶታል። ከዚህም ባለፈ አንዳንድ ጊዜ ግጭቶችን እናስወግዳለን። ጎረቤትዎ በርስዎ የተነሳ የመረበሽ ስሜት ይሰማቸዋል? የሚሰማቸው ከሆነ በአካል ወደነሱ መሄድ ሳይሆን፣ ይልቁንም ደብዳቤ ቢጽፉላቸው ይመረጣል። በትክክል የተረዳዎት መሆኑን ለማወቅ እርግጠኛ ካልሆኑና ከተጠራጠሩ፣ ጉዳዩን በትክክል ለመረዳት ደግመው ቢጠይቁ ይመረጣል።

## ተጨማሪ መረጃ ሊንኮች፣ አድራሻዎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ማብራሪያ ጽሑፎች

www.hallo-baselstadt.ch/am/gut-zu-wissen/zusammenleben-in-der-schweiz